# ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል
# 9 ኛ ሳምንት
# ያዕቆብ

**ዓላማ**

- ከያዕቆብ ሕይወት መልካምነት መማር ነው፡፡

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**

- «ቆይቼ እግዚአብሔርን ጠራሁት እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ፡፡» መዝ.39÷1

**ተጨማሪ ምንባባት**

- ዘፍጥ.27 - 32፣ እና 35፣

**መግቢያ**

- ባለፈው ትምህርታችን ያዕቆብ ዔሳው ለምግብ የሸጠውን ብኩርና ከአባቱ እንደተቀበለ ተምረናል፡፡ ዛሬ ተጨማሪ የያዕቆብን ታሪክና በሕይወት የነበሩትን መልካም ነገሮች እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ዔሳው ወንድሙን ያዕቆብን ለመግደል አሰበ፣ምክንያቱም የእርሱን ብኩርና ያዕቆብ ከአባቱ ወስዶ ነበር፡፡
- ይስሀቅና ርብቃም ተማክረው ወደ አጐቱ ላባ ቤት እንዲሸሽ አደረጉት፡፡ እግዚአብሔርም ያዕቆብ በሄደበት ሁሉ ከእርሱ ጋር ነበር አለ፡፡
- ወደ ላባ ሲሄድም በአንድ ሌሊት በመንገድ ተኝቶ ልዩ ሕልም አየ፡፡ መላእክትም ይወጡና ይወርዱ ነበር፡፡ ቦታውንም «ቤቴል» አለው፡፡ ትርጉሙም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ያችን ቦታ ለልጆቹ እንደሚሠጥ ቃል ገባለት፡፡
- ላባም ልያ እና ራሔል የተባሉ ሁለት ሴት ልጆች ነበሩት፡፡ ያዕቆብ ራሔልን ስለወደዳት 7 ዓመታት አገልግሎት ራሔልን እንዲሠጠው ጠየቀው ላባም ተስማማ፣ በሰባተኛው ዓመት መጨረሻም ላባ ታልቅ ናት እና ታላቅ እያለች ታናሽ አትሠጥም ብሎ ልያን ሠጠው፡፡ ያዕቆብም ተጨማሪ 7 ዓመታት ራሔልን ለማግኘት ሲል አገለገለ፡፡
- ወደ አባቱም ቤት ተመለሰ ከወንድሙ ከዔሳው ጋርም ሠላም ፈጠሩ 12 ልጆችም ነበሩት፡፡ እግዚአብሔር በቤቴል ያዕቆብን ዳግመኛ ባረከው ለአብርሃም እና ለይስሐቅ እሰጣችዋለሁ ያልኩት ምድር ለአንተና ለልጆችህ አወርሳለሁ ብሎም ቃል  ገባለት፡፡
- በመጨረሻም ሕይወቱም ያዕቆብ በዓለም በተከሠተ ታላቅ ረሀብ ምክንያት ከቤተሰቡ ጋር ወደግብፅ ወረደ፡፡ ሞቶም በግብፅ ተቀበረ ልጆቹም ለ400 ዓመታት በግብፅ ኖሩ፡፡ በኋላም በሙሴ መሪነት ከግብፅ ወጡ፡፡

**ጥያቄዎች፣** 1. ያዕቆብ የአባቱ በረከት ከተቀበለ በኋላ ወዴት ሄደ? ለምንስ ወደዚያ ሄደ፡፡

2. ያየው ሕልም ምን ነበር?
3. ሕልም ያየበትን  ቦታ ምን ብሎ ሰየመው?ትርጉሙስ ምንድነው?
4. ስንት ዓመት ላባን አገለገለው?
5. ያዕቆብ ስንት ልጆች ነበሩት? ያዕቆብ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ግብፅ ለምን ወረደ?
6. የያዕቆብ ተከታዮች በግብፅ ስንት ዓመት ኖሩ? ስለ ያዕቆብ ትዕግሥት:ይቅር ባይነት እና ታማኝነት አብራሩ፡፡

ይቆየን፡፡